# በኦታዋ ካናዳ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተደረገ

በግፍ የታሰሩ መሪዎቻችንን ለማስፈታት በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በኩል የተላለፈዉን ሕዝባዊ ጥሪ መሠረት በማድረግ በቶሮንቶ ፣ በሞንትሪያልና በኦታዋ የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያዉያን ሐሙስ FEBRUARY 15 ቀን 2007 ዓ.ም. በካናዳ ዋና ከተማ በኦታዋ PARLAMENT HILL ፊት ለፊት ተገኝተዉ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉ መሆኑ ታዉቋል:: ወያነ ៸ ኢህአዴግ በግንቦት 97 ምርጫ የደረሰበትን የፖለቲካ ክስረት ለማካካስ በማን አለብኝነት በፍትህ ስም ፍርደ ገምድል ብይን ለመስጠት ለየካቲት 12 ቀን 1999 ዓ.ም. / FEBRUARY 19, 2007 / የያዘዉን ቀጠሮ በጥሞና እንዲመረምር ለማድረግና ከኢፍትሐዊ ድርጊቱ ታቅቦ መሪዎቻችንን በአስቸኳይና ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ ለማስቻል የካናዳ መንግሥት ከሕዝባችን ጎን በመቆም አስፈላጊዉን ሁሉ ጫና እንዲያደርግ ሲሉ ሰልፈኞቹ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን የሆኑ የካናዳ የሕዝብ ተመራጮችን ጠይቀዋል::

የካናዳ መንግሥት የሕዝብ ተመራጭ የሆኑትና የኢትዮጵያን ጉዳይ በቅርበት ሲከታተሉ የቆዩት የተከበሩ ወ/ሮ ማርያ ሚና ከሰልፈኞቹ በፊት ቀደም ብለዉ ተገኝተዉ የተመለሱ በመሆኑ ምክኒያት በወቅቱ ንግግር ለማድረግ ሳይችሉ የቀሩ ቢሆንም ወኪላቸዉ አቶ ሬይሞን በዕለቱ ለሰልፈኞቹ ባደረጉት ገለጸ በኢትዮጵያ የሚካሔደዉን የሰብአዊ መብት ረገጣ ጠንቅቀዉ የሚያዉቅት መሆኑን በመጠቆም የታሰሩትን የፖለቲካ እስረኞች ለማስፈታት የካናዳ መንግሥት  የሚቻለዉን ሁሉ ኢንዲያደርግ የኢትዮጵያን ጉዳይ በቅርበት የሚከታተሉት ወ/ሮ ማሪያ ሚናም ሆኑ እርሳቸዉ በጽ/ቤታቸዉ በኩል አስፈላጊዉን ትብብር ሁሉ የሚያደርጉ መሆኑን አስገንዝበዋል:: የተከበሩ ሚስተር ስቶክዌል ዴይ የካናዳ ሚኒስቴር ኦፍ ፐብሊክ ሴፍቲ በበኩላቼዉ ለሰልፈኞቹ የጽሁፍ መልዕክት በመላክ ለሰብአዊ መብት መከበር ከኢትዮጵያዉያን ጎን እንደሚሰለፉ አስታዉቀዋል:: ሰልፈኞቹ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ስቴፈን ሃርፐር ያዘጋጁትን መልዕክትም ለጽ/ቤታቸዉ ገቢ አድርገዋል::

የቶሮንቶ ቅንጅት ጊዚያዊ አደራጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ የሱፍ ኡመር በበኩላቸዉ ባሰሙት ንግግር አስፈላጊዉን መስዋዕትነት ከፍለዉ ፍትሕ እንደ ዉሃ ለጠማዉ ሕዝባችን ድምጽ ለመሆን ከስድስት ሰዓት በላይ በአዉቶቡስ ተጉዘዉ ኦታዋ

ለሔዱትና ከዜሮ በታች 34 ዲግሪ ሴንት ግሬድ የነበረዉን ከፍተኛ ቅዝቃዜና ቁር ተቋቁመዉ በዚህ ታሪካዊ ሰልፍ ላይ የተገኙትን ኢትዮጵያዉያን በሙሉ አመሥግነዉ በካናዳ መንግሥት በኩል ከጊዜ ወደ ጊዜ እዬታዬ ያለዉን የዲፕሎማሲያዊ ጥረት አበረታች ዉጤት አስረድተዋል። አቶ የሱፍ ለሰልፈኞቹ ባሰሙት ንግግር ከአገር በላይ ምንም የለም፡ ክብራችንና ሞገሳችን አገራችን ስለሆነች ኃላፊነት የማይሰማቸዉ የወያኔ መሪዎች አገራችንን እያዋረዱና ሕዝባችንን እያሰቃዩ በዘር በሃይማኖት እዬከፋፈሉ ግፍ ሲፈጽሙ ዝም ብሎ ማዬት የታሪክ ተወቃሽነትን ስለሚያስከትል ሁላችንም መሪዎቻችን እስኪፈቱና ሕዝባችን ነጻነቱን እስኪቀዳጅ ድረስ ተደራጅቶ መታገል ይገባናል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዉ ተናግረዋል። አያዘዉም የቶሮንቶ ቅንጅት ጊዚያዊ አደራጅ ኮሚቴ ከተዋቀረ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ያከናወናቸዉን ተግባራት በመዘርዘር በቅርቡ በቶሮንቶ አጠቃላይ ሕዝባዊ ስብሰባ በመጥራት የቅንጅቱ የበላይ አመራር አካላት በተገኙበት ቅንጅት ቶሮንቶ በሕዝባዊ መሠረት ላይ በአዲስ መልክ እንደሚዋቀር አብራርተዋል።

ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ይህንኑ አጋጣሚ በመጠቀምም የወያኔ አቃቤ ሕግ የሆነዉና ቃሊቲ በታሰሩ መሪዎቻችን ላይ የፈጠራ ክስ በመመስረት አስቂኝና አስገራሚ የሆነ የሃሰት ማስረጃ ሲያቀርብ የቆዬዉ አቶ ሽመልስ ከማል እና የፍትህ ሚኒስቴር ነኝ የሚለዉ ዶ/ር ሐሺም መሐመድ ባሳለፍነዉ ሳምንት ዉስጥ ከፌብሩዋሪ አስራ ዘጠኙ የብይን ቀን ጋር በተያያዘ ስዉር በሆነ ተልዕኮ ኦታዋ ካናዳ መምጣታቸዉን በብርቱ በመቃወም ግለሰቦቹ ለአምባገነኑ የወያኔ/ኢሕአዴግ ቡድን የሕግ ሽፋን ለመስጠት ሲሉ በመፈጸም ላይ ያሉትን ታሪክ ይቅር የማይለዉ ሕገወጥ ድርጊት በአስቸኳይ እንዲያቆሙ ሲሉ ጥሪያቸዉን አስተጋብተዋል።

በሰልፉ ላይ የቀድሞ ታዋቂ ኢትዮጵያዉያን አትሌቶች የግል ጋዜጠኞች እና የአርቲስት ደበበ እሸቱን ልጅ ጨምሮ በቃሊቲ በእስር ላይ የሚገኙ የመሪዎቻችን ቤተሰቦች እና የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ተገኝተዋል።
ሰልፈኞቹ በወቅቱ ካሰሚቸዉ መፈክሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፦

- የሃሰት ክስ ያብቃ !
- የህሊና እስረኞችን ማስፈታት ለሃገራችንና ለሕዝባችን ሰላም ወሳኝ ነዉ !
- የቅንጅት መሪዎችና ሌሎችም የህሊና እስረኞች ባስቸኳይ ይፈቱ !
- የእርቅና የሰላም ጉባኤ አሁኑኑ ይደረግ !

- ወያኔ የሚያስተላልፈዉን ፍርደ ገምድል ዉሳኔ በቀላሉ የምንመለከተዉ አይሆንም!
- በሃገርና በወገን ላይ ያንዣበበዉን አደጋ ማስቀረት የዜጎች ሁሉ ታሪካዊ ድርሻ ነዉ !
- ታሪካዊ ግዴታችንን በተቀነባበረ ሰላማዊ ተቃዉሞ እንወጣ !
- ለፍትህ ዘብ መቆም ታሪካዊ ግዴታ ነዉ !
- አንድ አገር አንድ ሕዝብ አንድ ባንዲራ !
- ሰብአዊ መብት የተፈጥሮ በረከት ነዉ !
- መሪዎቻችን በወያኔ ካንጋሩ ፍርድ ቤት ፍትሕን አያገኙም !
- ካናዳ ከገዳዮች ጋር ሳይሆን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንድትሰለፍ እንጠይቃለን !
- ካናዳ በኢትዮጵያ ፍትሕ ዲሞክራሲና ሰላም እንዲሰፍን ደግፊ !
- ሰላም ለሕዝባችን ! ሰላም ለአገራችን ! የሚሉና ሌሎችም ይገኙባቸዋል::

በዕለቱ የተቀረጹት ንግግሮችና ግጥም እንዲሁም ፎቶግራፎች ከዚህ ጽሁፍ ጋር ተያይዘዋል::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
ቅንጅት ቶሮንቶ ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ

kinijittoronto@gmail.com
Tel. 416 203 9204